# የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እነማን ናቸው ?

በመንፈሳዊ ስብሰባና የገንዘብ አስተዋ
ጽኦ በቃል ሳይሆን በተግባር ተካፋይ የ
ሚሆኑ ምእመናን ሁሉ የቤተ ክርስቲያ
ን ሰዎች ተብለው ይጠራሉ ይህንን የሚ
ጽሙ አግኞች በሙሉ እንደ አንድአ
ባል ይቆጠራሉ ፤ ክርስቶስ የቤተ ክርስ
ቲያን ራስ ሲሆን በርሱ የሚያምኑና እ
ርሱን የሚከተሉ አካላት ተብለው ተሰ
ይመዋል በተጨማሪም ክርስቶስ የቤተ
ክርስቲያን ማዕዘንና ጉልላት ሲሆን ም
እመናን ደግሞ ሕንፃ ተብለዋል “ እና
ንተ የእግዚአብሔር መቅደስ ናችሁ ”
ተብሎ ተጽፏልና ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቤቤተ ክርስቲያ
ን የሚሠሩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እነ
ማን ናቸው? ብንል የተለያዩ የቤተ ክር
ስቲያን ሰዎችን እናገኛለን እነዚህም ለ
አገልግሎትና ለሥራ የተጠሩ ናቸው ጥ
ሪውም ዲያቆን ፣ ቄስ ፣ መነኩሴ ፣ መን
ፈሳዊ መዝሙር ዘማሪ ፣ ጳጳስና ኤጲስ
ቆጶስ ሆነው ሕዝብን እንዲያገለግሉ ነ
ው ።

ስለዚህ ታላቁ መጽሐፍ እንደሚለው
አገልጋይ ካህን እንዲህ ሊሆን ይገባዋል
“የማይነቀፍ ፣ የአንዲት ሚስት ባል ፣
ልከኛ ፣ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የ
ሚሠራ ፣ እንግዳ ተቀባይ ፣ ለማስተማ
ር የሚበቃ ፣ የማይሰክር ፣ የማይጨቃ
ጨቅ ገር የሆነ ፣ የማይከራከር ፣ ገንዘብ
የማይወድ ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ
እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስ
ተዳድር ሰው መሆን አለበት የራሱን ቤ
ት ማስተዳደር ካለወቀ ግን የእግዚአ
ብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠ
ብቃት ይችላል” ይላል 1ኛ ጢሞ. 3 ከ
ቍ. 3-5

በእርግጥም ለሥራና ለአገልግሎት
የተጠሩ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች
ሁሉ መጀመሪያ እራሳቸውን መግዛትና
ቤተሰባቸውንም በሚገባ ማስተዳደር
ይፈለግባቸዋል በዚህ ከተፈተኑ የእግዚ
አብሔርን ቤተ ክርስቲያን ሊያስተዳ
ድሩና ለሕዝቡም ጥሩ አገልግሎት ሊሰ
ጡ ይችላሉ በምሳሌነታቸውና በአሠራ
ራቸውም ብዙ አግኞችን ይስባሉ የቤተ
ክርስቲያንም ሰዎች ናቸው መባል የሚ
ገባቸው እንዲህ ያሉት ናቸው ።

በሌላ አንፃር ደግሞ በክርስቶስ ሳያ
ምኑና ሳይጠሩ በቤተ ክርስቲያን የሚገ
ኙ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ናቸው
ማለት አይቻልም ለምሳሌ በቤተ ክርስ
ቲያን ጉልላት ላይ ቆሞ የሚጮህ ቍራ
የቤተ ክርስቲያን አፍራሽ እንጂ አገል
ግሎት ሰጭ አይደለም ይህንንም አነጋ
ገር እውነት የሚያደርገው በድኅነት ሳ
ሉና ሥራ ሲያጡ የቤተ ክርስቲያን ሠራ
ተኛ መስለው ይታያሉ ሥራ ሲያገኙና
ሲመቻቸው ግን ኖኅ እንደላከው ቍራ
እንደጠፉ ይቀራሉ በዚህ አኳኋን ክርስ
ቲያን ሳይሆኑ መስለው የሚኖሩ ሁሉ
እንደ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች አይቆጠሩ
ም ።

ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ የኢትዮ
ጵያን ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ከሚያ
ጠቁአት ምክንያቶች አንዱ የአስመሳዮ
ች መብዛት እንደሆነ የተጨበጡ ማስረ
ጃዎች ማቅረብ ይቻላል ይኸውም በዲ
ቁና ፣ በቅስናና በምንኩስና ስም ሲያገለ
ግሉ ከኖሩ በኋላ ኃላፊነታቸውን ክደው
ና በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን መ
ልካቸውን ለውጠው የሚኖሩ እንዳሉሁ
ላችንም ስለምናውቅ ከዚህ የበለጠ መ
ረጃ አያሻም ይኸውም መጀመሪያ የተ
ሰማሩበትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ሲ
ያቅታቸው ዓላማ ቢሶችና ሁሳበ ስንኩ
ሎች ከመሆናቸው የተነሣ በሌላ የሥራ
መስክ እንኳን ቢሰማሩ እምነት አይጣ
ልባቸውም ።

ይህ ከሆነ የቤተ ክርስቲያንን ሰዎች
የት ማግኘት ይቻላል የሚል ጥያቄ ይቀ
ርብ ይሆናል መልሱም የቤተ ክርስቲያ
ንን ሰዎች “ከፍሬያቸው ታውቁዋቸዋላ
ችሁ” ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ከ
ፍሬያቸው ልናውቃቸው እንችላለን።ይ
ህም ማለት ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብ
ያተ ክርስቲያናት ጋር የጠበቀ ግንኙነት
እንዲኖራት የሚጥሩ ፤ ስለ ዓለም ሰላም
ስለ ሰው ልጅ መብትና እኩልነት ፤ ስለፍ
ትሕና ስለዘር አድልዎ የሚታገሉ ናቸ
ው ።

የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የት ይገኛሉ
ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን
በቅድሚያ ሙሉ የክርስትና ትምህርት
እምነትና የስብከት ዘዴ ፣ የነገረ መለኮ
ትና ፣ የአሥተዳደር ፣ እንዲሁም ሥነሥ
ሥርዓት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶ
ች ሲኖሯት ሰዎች ለአገልግሎትና ለሥ
ራ ከዚያ ይጠራሉ ።

ይህ ከሌለ ግን እንደ ዝንጀሮ ከየዋሻ
ው እየተጠሩ የሚመጡት ሁሉ የቤተ ክ
ርስቲያን ሰዎች አይደሉም እንደነዚህ
ያሉት ገና ጠጠር ሲወረወር ወደ ገደላ
ቸው ዘለው ከመግባት በቀር ቤተ ክርስ
ቲያን ችግር ሲደርስባት መከራም ሲመ
ጣባት የችግሯም ሆነ የመከራዋ ተካፋ
ዮች አይሆኑም የክርስቶስን መስቀል ተ
ሸክሞ የመከተል ልምምድ የላቸውምና
ይህም ብቻ አይደለም የፖለቲካ በር ሲ
ዘጋባቸው የሃይማኖት ሰዎች ነን ይላሉ
የሃይማኖት በር ሲጠብባቸው ደግሞ የ
ፖለቲካ ሰዎች ነን እያሉ እንደ ሌሊት
ወፍ አቋማቸውን ያለዩና ዓላማ ቢሶች
የሆኑ በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ አ
ልፎ አልፎ እንደማይጠፉ ግልፅ ነው ።
እንደነዚህ ያሉት ለክህነት አገልግሎት
እንደማይበጁ ሁሉ ለፖለቲካም አይበ
ጁም ሌላው ይቅርና ራሳቸውን እንኳን
እንደማይጠቅሙ ሐቅ ስለሆነ ዓላማቸ
ውን ይለዩ እንላለን ።

ለምሳሌ የሌሊት ወፍ በየቤተክርስቲ
ያኑ ጣሪያ ላይና በየማዕዘኑ ትኖራለች
በጥርስዋ አይጦችን በክንፍዋ ወፎችን
ስለምትመስል የማንኛው አባል መሆን
ዋ ካለመታወቁም ሌላ ግድግዳዎችንና
ጣሪያዎችን እየቦረቦረች በቤተ ክርስቲ
ያን ላይ ታላቅ ጉዳት ታደርሳለች በተ
ጨማሪም ዕቃዎችን ታበላሻለች እንጂ
የምትሰጠው አገልግሎት የላትም እን
ዲሁም በቤተ ክርስቲያን የምናያቸው
ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ናቸው ለ
ማለት አንደፍርም ምክንያቱም በውስ
ጥዋ የሚገኘውን ፍሬ ይበላሉ ፍሬ ፣ም

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል

ፈራበትን መንገድ ግን ሲፈልጉ አይ ታዩም ራሳቸውን ከማገልገል በቀር ሌ ላውን አያገለግሉም ። ሰዓታት ፡ በ ግርግርታ ፡ ዳዊት ፡ በሹልክታ ስ ለለመዱ ስበኩ አስተምሩ ሲሏቸው ልዩ ልዩ ምክንያትን እየፈጠሩ ሠራተኛው ን እየከፋፈሉ ሰላም እንዲጠፋ ከማድ ረግ በስተቀር የሥራው ተባባሪ አይሆኑ ም ።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ማ ንነታቸውን በምን መግለጽ ይችላሉ ? የቤተ ክርስቲያን ሰዎች መሆናቸውን የሚገልፀው ቅድስናን ፡ ግብረገብነትን ትዕግሥትን ፡ እምነትን ፡ ፍቅርን ፡ ሰላ ምን አድልዎ የሌለበትን አስተዳደር ፡ ትክክለኛ ፍርድን ፡ እውነትንና እኩል ነትን ፡ ራሳቸው ሠርተው ሌላውም እን ዲሠራ ያደረጉ እንደሆነ ነው ።

የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እነማን ናቸ ው? የሚለውን ጥያቄ ለማጠቃለል ስለ ጌታና ስለ ስሙ እስከ ሞት ድረስ የሚ መሰክሩ ናቸው በተጨማሪም መከራን የሚቀበሉ እንጂ ከመስቀሉ የሚሸሹ አ ይደሉም በዚህ አንፃር የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በነፃ እን ደተቀበሉ በነፃ ከመስጠት በቀር በእግ ዚአብሔር ቃል ሊነግዱና ሊሸቅጡ አይ ገባም ‘‘በጸጋ የወሰዳችሁትን በጸጋ ስጡ’’ ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

ጎንሣኤ መድሎት
ቁጥር 15
1971